# በስዊዘርላንድ እና ኦስትሪያ የምንኖር

# ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የ አቋም መግለጫ!

እኛ በስዊዘርላንድ እና ኦስትሪያ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ላለፉት 27 ዓመታት በሃገራችን ተንሰራፍቶ የነበረው በትግራይ ህዝብ ነፃነት ግንባር የሚዘወረው ፀረ ህዝብ አፋኝና ኢዴሞክራሲያዊ ኣስተዳደር በሕዝባዊ ትግል ተወግዶ በሃገራችን የሰላም የዴሞክራሲና የ እኩልነት ኣየር መተንፈስ የጀመረችበት የለውጥ ሂደት እያጋጠሙት ባሉት መሰናክሎችና በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እኔ ካልገዛሁዋት ኢትዮጵያውያን አፈርሳታለሁ በሚል እብሪት የሕወሃት እብሪተኛ ቡድን በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ላይ በኖቬምበር 4 የፈፀመውን ክህደት እና ጭፍጨፋ በተመለከተ  በጄኔቭ የኢፌዴሪ ቋሚ መልዕክተኛና ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ዘነበ ከበደ ጋር በ ኖቬምበር 21 ቀን 2020 ዓ /ም እና በ ኖቬምበር 28 ቀን 2020 ዓ /ም የበይነ - መረብ ውይይቶች አካሂደናል።

በ 2018 ዓ/ም እጅግ ተስፋ ሰጭ ሆኖ በተጀመረው የለውጥ ሂደት የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ተፈተው ሃሳብን በነፃነት የማቅረብ መብቶች ተከብረው የፖለቲካ ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታት መንግስት ከተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ጋር በጠርጴዛ ዙሪያ በተደጋጋሚ ለውይይት መቀመጥ የጀመረባቸው 2 ዓመታት አሳልፈናል ። ባሳለፍናቸው 2 ዓመታት ሃገራችን ከጎረቤት ሃገራት ጋር ባሰፈነችው ሰላም ጠቅላይ ሚኒስትር ዓቢይ አህመድ የኖቤል የሰላም ሽልማት አሸናፊ ከመሆናቸውም በላይ ላለፉት 50 ዓመታት እርስ በርስ በመናቆር የሚታወቀው የፍሪቃ ቀንድ መሪዎች ለመጀመሪይ ጊዜ እርስ በርስ ተግባብተው መደጋገፍ የጀመሩበት ወቅት ላይ እንገኛለን።

ይህ ተስፋ ሰጭ ጅምር በሃገር ውስጥ የበዙ ተግዳሮቶች ገጥመዉታል ። ከሁሉም የከፋው ተግዳሮት በየቦታው የሚነሱ ዘር ተኮር ግጭቶች እና አንድን ዘር ወይም የሃይማኖት ወገን ለይቶ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ናቸው። በነዚህ ጥቃቶች እጅግ ብዙ የወገኖቻችን ሕይወት ጠፍትዋል ። እጅግ ብዙ ንብረት ወድምዋል። ከነዚህ ዘር ተኮር ጥቃቶችና ገጭቶች ጀርባ ያሉ እኩያን ሃይሎች ከስልጣን በተባረረው የትግራይ ህዝብ ነፃነት ግንባር የሚዘወሩ ሀይሎች መሆናቸው የአደባባይ ሚስጥር ቢሆንም መንግስት ተመጣጣኝ እርምጃ ወስዶ ከማስቆም ይልቅ በሆደ ሰፊነት ነገሮችን ለመያዝና በውይይት ለመፍታት የሄደው ርቀት ውድ ዋጋ አስከፍሎናል። ዛሬም የገባንበት ወታደራዊ ግጭት ይህን የመንግስት ሆደ ሰፊነት እንደድክመት የቆጠሩ የትናንት ገዥዎቻችን እብሪት የወለደው ነው ብለን እናምናለን።

ሕወሃት ለ27 ዓመታት በፈፀማቸው አስቃቂ ወንጀሎችና በፈፀማቸው ሃገር የሚያራቁቱ ዘረፋዎች  ለፍርድ በመቅረብ ፋንታ በሰላም ትግራይን የማስተዳደርና ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ጋር የለውጡን ሂደት በማፋጠን ለሃገር ሁለንተናዊ እድገት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን የመሰለፍ እድል ቢሰጠውም ይህን እድል ከመጠቀም ይልቅ በሕዝብ ተቃውሞ ያጣውን ሥልጣን በ አመፅና በግርግር ለማስመለስ የቆረጠው ሕወሃት ላለፉት 2 ዓመታት የቀረቡለትን የሰላም ጥሪዎች ሁሉ ረግጦ በአመፃ መንገድ ቀጥሎበታል ።

በዚህ ረገድ በዓለም ላይ በተከሰተው የኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት ምርጫው  እንዲራዘም ፓርላማው ሲወስን ሕወሃት ይህን ሕጋዊ ውሳኔ ረግጦ የራሱን ምርጫ አካሂዳለሁ አለ። ሕወሃት የፓርላማውን ውሳኔ ረግጦ የራሱን ምርጫ አካሂዳለሁ ማለቱ የሚያስከትለው መዘዝ ያሳሰባቸው የሃይማኖት መሪዎችና የሃገር ሽማግሌዎች መቀሌ ድረስ በመጉዋዝ ልመናቸውን ቢያቀርቡም ሕወሃት በትእቢት እና ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በጎደለው መልኩ ኣዋርዶ መልስዋቸዋል። እራሱ ባካሄደው ምርጫ እራሱ ባቀረባቸው እጬዎች የተዋቀረውን ፓርላማ ውሳኔዎች እንኳን ለመቀበል እና ለመተግበር ኣሻፈረኝ ብሎ እራሱ ቀምሞ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጫነውን ሕገ መንግስትም ጭምር ረግጦ  በክልሉ ኢ-ህገ መንግስታዊ ምርጫ ኣካሂዶዋል። የፌዴራል መንግስቱንም ኣላውቀውም ብሎዋል።

ይህን ሁሉ አድርጎም መንግ ስት ለትግራይ ሕዝብ የኮቪድ መከላከይ ጭምብል እንጂ ጥይት አልልክም በማለት ለሰላም በሰላም ለመስራት ነው የሞከረው።

በኖቬምበር አራት ለሊት ግን ሕወሃት ለ 21 ዓመታት በትግራይ በረሀ ሰፍሮ ትግራይና እና ኢትዮጵያን ሲጠብቅ በነበረው የሰሜን እዝ ላይ ያልታሰብ ጥቃት በመፈጸም ብዙ ወታደሮችና የጦር መሪዎችን በተኙበት ጨፍጭፎ ለሃገር መጠበቂያ በሰራዊቱ እጅ የነበሩ ከፍተኛ መሳሪያዎችን ዘርፎ አፈሙዙን ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ በማዞር ጦርነት ከፈተ።

ይህ ጦርነት የሕወሃትን እብሪት ያሳየ ነው። ይህ ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ የተፈፀመ ክህደት ነው። ይህ ክህደት ታሪክ ይቅር የማይለው የማይሽር ጠባሳ ነው። ሃገራችን ኢትዮጵያ ናት ከጀርባዋ የተወጋችው። በመሆኑም የዚህ ስብሰባ ተካፋዮች

1 - ይህን ሕወሃት በሃገራችን ላይ የፈፀመውን ክህደትና የከፈተውን ጦርነት አጥብቀን እናወግዛለን።

2 - የኢትዮጵያ መንግስት የመከላከይ ሰራዊቱን አንቀስቅሶ ይህን ጥቃት ለመቀልበስና ህግና ስርዐት ለማስከበር እያደረግ ያለውን ጥረት ከልብ እንደግፋለን ፣ በዚህ ረገድም ከመንግስት ፣ ከመከላከይ ሰራዊታችን እና ከመከላከይ ሰራዊታችን ጎን ተሰልፈው እየተዋደቁ ካሉ ፋኖዎች ፣ ሚሊሺያዎችና የልዩ ሀይል ኣባላት ጎን በፅናት በመሰለፍ በኣስፈላጊው መንገድ ሁሉ እገዛችንን እንደምናደርግ እናረጋግጣለን።

3 - መንግስት በእብሪት ያበጠውን የሕወሃት ፅንፈኛ ና አረመኔ ቡድን ለፍርድ እንዲያቀርብ እንጠይቃለን።

4- ላለፉት አርባ አምስት ዓመታት ሃገራችንን እና የ አፍሪቃ ቀንድን በሽብር ሲያተራምስ የኖረውን ሕወሃት በሽብርተኝነት በመፈረጅ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ላለፉት አርባ አምስት ዓመታት ለፈፀማቸው ወንጀሎች በሙሉ ለፍርድ እንዲያቀርበው እንጠይቃለን

5- እብሪተኛውና አረመኔው የሕወሃት ቡድን በመከላከያ ሰራዊታችን የደረሰበትን ሽንፈት ለመበቀል ከማይ ካድራ ነዋሪዎች ውስጥ የትግራይ ተወላጅ ያልሆኑትን በተለይም የ አማራ ተወላጆችን በመታወቂያ እየለየ በዱላ በድንጋይ በገጀራና በመሳሰሉት በመጨፍጨፍና በገመድ ጭምር በማነቅ ከስምንት መቶ በላይ በሆኑ ወገኖቻችን ላይ ያካሄደውን ጀኖሳይድ አጥብቀን እናወግዛለን።

6 - መንግስት የማይካድራን ጨፍጫፊዎች የገቡበት ገብቶ በማደን ለሕግ እንዲያቀርብ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

7 - አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን አጥኚዎችን ስፍራው ድረስ በመላክ በተጨባጭ ማስረጃ ወንጀሉን እና የወንጀሉን ፈፃሚዎች በመለየት ላቀረቡት ፈጣን ሪፖርት እናመሰግናለን።

8 - መንግስት ይህን የማይካድራ ጭፍጨፋ የዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ እንዲዘግበውና የገለልተኛ ወገኖችም ጭምር አጥንተውት በዓለም አቀፍ ደረጃ እትዮጵያ ውስጥ ላለፉት ሰላሳ ዓመታት መዋቅራዊ በሆነ መልክ የሚካሄደው የዘር ወይም ኤትኒክ ፖለቲካ ሃገራችንን ከሩዋንዳ ወደባሰ ጥፋት እየመራት እንደሆነ ግንዛቤ እንዲወሰድበት እንዲያደርግ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

9 - እብሪተኛውና አረመኔው የሕወሃት ቡድን ለራሱ ስልጣንና የሃብት ዘረፋ ለማመቻቸት የለኮሰው ጦርነት እራሱን መልሶ ሲለበልበው ጎረበት ሃገራትን ወድ ግጭት ስቦ ለማስገባትና ምስራቅ አፍሪቃን የጦርነትና ሽብር ቀጠና ለማድረግ በጎረቤት ሃገር ኤርትራ ላይ በተከታታይ የፈፀማቸውን የሮኬት ጥቃቶች አጥብቀን እናወግዛለን። የ ኤርትራ መንግስት ምንም እንኳዋን ለተፈፀመበት ጥቃት አፀፋውን የመመለስ መብት ቢኖረውም የሕወሃት ትንኮሳ ቀጠናዊ ግጭት ለመቀስቀስ መሆኑን በመረዳት አፀፋ እርማጃ ላለመውሰድ በመወሰኑ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

10 - የስዊዘርላንድ መንግስትና በስዊዘርላንድ የሚገኙ የዲፕሎማቲክ ኮምዩኒቲ አባላት እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች ኢትዮጵያ እያካሄደችው ያለችው ሕግ የማስከበር እንቅስቃሴ መሳካት ለኢትዮጵያ ፣ ለምስራቅ አፍሪቃና ለመላው የቀጠናው ሃገራት ሰላም ያለውን ወሳኝ ሚና በመረዳት ከኢትዮጵያ መንግስት ቆን በመቆም ለሰላምና ለሕግ የበላይነት መከበር የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ ጥሪያችንን እናቀርባለን። በዚህ ረገድም የድርሻችንን ለመወጣት የምንንቀሳቀስ መሆኑን እናረጋግጣለን።